# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

መልእ. ሣ. ቁ. 8)02፤ ስልክ ቁ. 06-08-*5፤ "-00-*5፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

ነሐሴ "1 ቀን፥ 09)(4 ዓ. ም.

ለአቶ ምርጫው ስንሻው፤
የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ሙሴ (President)፤
መ.ሣ.ቁ. 9-1-5-3-5፤
ዋሽንግተን፥ ዲ.ሲ. 2-0-0-9-0፡፡

ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ በእግዚአብሔር ስም አቀርባለሁ፡፡

በነፋስ ድምፅዎ (Radio) አማካይነት በተላለፈው ጥሪ መሠረት፡ ሰኔ 06 ቀን፥ 09)(4 ዓ. ም. (June 23, 2002)፡ በዋሽንግተን ሓውልት አደባባይ በተከበረው “የኢትዮጵያዊነት ቀን” ላይ በመገኘቴ፡ ሓምሌ 8 ቀን፥ 09)(4 ዓ. ም. (ሐምሌ 8 ቀን 1994 ዓም ተብሎ፡ በፈረንጆቹ አነዝ) የተጻፈ የ“ምስጋና” ደብዳቤዎ፡ ዘግይቶ፡ በነሓሴ 7 ቀን፥ 09)(4 ዓ. ም. ለአገልግሎታችን ጽ/ቤት ደርሷል፤ ለእኔም ቀርቦልኝ፡ ተመልክቼ፡ ይህን መልስ የጻፍሁልዎ፡ ለኢትዮጵያዊነታችን አንዱ መታወቂያ የኾነው፡ የንግሥታችንና እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፍልሰታዋ ሱባዔ እንዳበቃ መኾኑን ስገልጽልዎ፡ “እንኳን፡ ለብርሃን ትንሣኤዋ አደረሰን!” እያልሁ ነው፡፡ ከላይ ስለተጠቀሰው ደብዳቤዎ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ኢትዮጵያዊነታችን የተመሠረተው፡ በእግዚአብሔር ስለኾነ፥ እግዚአብሔርም፡ እውነት ስለኾነ፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የምናስበው፥ የምንናገረውና የምናደርገው ኹሉ፡ ከዚች እውነት የተለየ እንዳይኾን፡ በብርቱ ልንጠነቀቅበት የሚገባ መኾኑን፡ ኹላችንም የምናምንበት ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ውጭ ኾነን፡ የተቃራኒው ሓሰት፡ ወገኖችና አገልጋዮች ኾነን ስንገኝ ግን፡ ኢትዮጵያዊነታችን ይቀራል፡፡ ስለዚህ፡ “ኢትዮጵያዊነታችንን ይጐዳል!” ብለን የምንገምተውን፡ ማናቸውንም ነቍጥ ሳይቀር፡ አቃልለን ልናልፈው የማይቻልና የማይገባ መኾኑን፡ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ በደብዳቤዎ ውስጥ፡ ሊስተካከል የሚገባው፡ እውነት ያልኾነ ነገር ስላገኘሁ፥ እርስዎም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ከኾኑ፡ ስለእውነት የሚገለጸውን ኹሉ፡ ሰምተው ለመቀበል፡ እንደሚደሰቱ እንጂ፡ ቅር ይልዎታል ብዬ ስለማላስብ፥ ትምህርትም ይኾንዎት ዘንድ፡ መልሴን ሰፋ አድርጌ እንድጽፍልዎ ተገድጃለሁ፡፡ ይህም፡ “በኢትዮጵያ ቀን” በዓል ላይ፡ *“በክብር ተናጋሪነት ተገኝተው”* የሚለው ሓረግ፡ ትክክልና እውነት ባለመኾኑ፡ ስለዚሁ ስሕተት የሚያትተው፡ ከዚህ የሚከተለው ማብራሪያ ነው፡፡

በመጀመሪያ ነገር፡ እኔና የአገልግሎት ባልደረቦቼ፡ በዚያ በዓል ላይ የተገኘነው፡ ለማናቸውም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፡ በነፋስ ድምፅዎ ያደረጉትን አጠቃላይ ጥሪ ሰምተንና ተቀብለን፡ በአገልግሎታችን ስም ለመካፈል እንጂ፡ ለባልደረቦቼ፡ በጋራ፥ ወይም፡ በግል፡ ለእኔ፡ ልዩ ጥሪ ደርሶን እንዳልነበረ፡ እርስዎም ያረጋግጡታል፡፡ ምናልባት፡ በዚያን ጊዜ፡ የዚህ አጻጻፍዎ መንፈስ፡ በእውነት ከልብዎ ኖሮ ቢኾን፡ እኔን፡ በዚያው በቦታው ላይ፡ በ*“ክብር ተናጋሪነት”* ለመጋበዝ ያስችልዎ በነበረው ዕድል፡ በተጠቀሙ ነበር፤ ይህንም እንኳ ለማድረግ አለመፈለግዎን፡ በዕለቱ አሠራርዎ፡ የደረሰው ኹኔታ፡ በገሃድ አሳይቷል፡፡

...2

ይኸውም፡ ለዚያን በዓል፡ በኢትዮጵያዊነታቸው፡ የክብር ተናጋሪዎች እንዲኾኑልዎ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ ወይም በቤተ ምልክናው፥ ወይም በቤተ ክህነቱ ዘንድ "የሚታወቁ ናቸው" ብለው፡ ጋብዘዋቸው፡ ጥሪዎን ሳያከብሩልዎ የቀሩ ሰዎች ስለነበሩ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታዝዤ፡ እበዓሉ ላይ የተገኘሁትን፡ እኔን፡ የእነዚያን፡ ተጋብዘው የቀሩትን ሰዎች ቦታ እንደተካሁ ቆጥረው፡ *"የክብር ተናጋሪነቱን"* ደረጃ ሊሰጡኝ ይችሉ የነበረ ሲኾን፡ በዚያን ጊዜ፡ በእኔ ላይ ያለዎት አስተሳሰብ፡ ቅን ባለመኾኑ፡ ይህን በመሰለው ቀላል ዕድል ለመጠቀም እንኳ፡ ፈቃደኛ ሳይኾኑ መቅረትዎ ነው፡፡

በመጨረሻ፡ በበዓሉ ላይ፡ ከሰማኋቸው ንግግሮች መካከል፡ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ውጪ የኾኑ፡ አንዳንድ ኃይላተ ቃላት ተሠንዝረው ስለነበረ፡ የኹሉም ተናጋሪዎች ድርሻ ካበቃ በኋላ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት፡ ከመሠረቱ በመነካቱ፡ እርስዎ ጭምር ተቈርቍረው፡ የተቃወሰውን ለማቃናት፡ ለእነዚያ፡ አፍራሽ ቃላት፡ ተገቢውን መልስ በመስጠት፡ በጥቂቱም ቢኾን አብራራ ዘንድ፡ "እኔንም ይጋብዙኛል" ብዬ ጠበቅሁ፤ ነገር ግን፡ ምንም ዓይነት ምልክት ሳላይ ቀረሁ፤ ስለዚህ፡ የሚቻል ቢኾን፡ እርስዎ እንዲያነጋግሩኝ፡ ራሴ ልኬብዎ ሲመጡልኝ፡ ጥቂት ቃል ለመናገር እንዲፈቅዱልኝ ጠየቅሁዎ፤ እርስዎም፡ ጥያቄዬን ስለተቀበሉት፡ ከመድረኩ ላይ ወጥቼ፡ ገና መናገር ስጀምር፡ የኾነውን ኹሉ፡ በአካባቢያችን የነበሩት፥ በተለይ እርስዎ፡ ደህና አድርገው ያውቁታል፡፡ እንደሚያስታውሱት፡ በመድረኩ ላይ ኾኜ፡ ገና ቁም ነገሩን መናገር ስጀምር አልነበረምወይ፡ "በቃ! ንግግርዎን ያቁሙ!" የተባልኩት? የወጠንሁትን ዐረፍተ ነገር ለመጨረስ እንኳ እስኪያቅተኝ ድረስ አልነበረምወይ፡ ንግግሬን እንዳቋርጥ የተወተወትሁት? ቀልቤን በመንሣት፡ ንግግሬ፡ ፈሩን እንዲለቅ ለማድረግ፡ ኾን ተብሎ የተፈጸመ ሴራ ይመስል እንደነበረ ይዘነጉታል? ወዲያው፡ ለጥቂት ደቂቃዎች የቆየችውን፡ ያችን ንግግሬን "ካላቆምህ፡ የመናገሪያውን ገመድ ልንነቅለው ነው!" የሚል፡ የዛቻ ያህል፡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ፡ መልእክቴን አቋርጬና ባጭር ቀጭቼ እንዳጠቃልል ግድ ኾነብኝ፡፡ ለነገሩ፡ ትእዛዙ ይደርሰኝ የነበረው፡ ከእርስዎ በሚሰጥ መልእክት ስለነበረ፡ ከማነኛችንም ይበልጥ፡ የኾነውን ኹሉ እርስዎ ያውቁታል፡፡ እኔ ግን፡ በትእግሥት ጸንቼ፡ በንቃት ያዳምጥ ለነበረው ሕዝብ፡ ቁም ነገሩን ሳስተላልፍ ችያለሁ፤ ይህም ሊኾን የቻለው፡ በበዓሉ ላይ ተገኝቼ፡ እርስዎ ሳይቀሩ፡ *"ለተሰብሳቢው ሰው፡ ያስተማሩልን ትምህርት፡ እጅግ ጠቃሚ ነበር፤"* ብለው፡ በደብዳቤዎ ያሞገሷትን፡ ያችን አጭር መልእክት እንዳደርስ፡ መንፈስ ቅዱስ ጣልቃ ገብቶ በፈጸመው ኃይል በመኾኑ፡ አምላከ ኢትዮጵያን አመሰግነዋለሁ፡፡

ይህን ያልሁት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ በዚህ ጉዳይ፡ የመንፈስ ቅዱስ እጅ የነበረበት መኾኑን ስላመንሁበት ነው፡፡ ለዚህም፡ ያ፡ "የኢትዮጵያዊነት ቀን" የዋለበት ዕለት፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት፡ የመጨረሻው ታላቁ በዓላችንና የኪዳነ ምሕረት መታሰቢያ፡ ከሰንበተ ክርስቲያን እሑድ ጋር ተጣምሮ የሚከበርበት ቀን መኾኑን፡ ለንግግሬ መግቢያ ማድረጌና በዚያ በዓል ላይ ለመገኘት አንዱ ዋነኛ ምክንያታችን፡ ይኸው መኾኑን መግለጼ፡ በልዩ ማስረጃነት ሊወሳ ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት፡ እኔም ኾንሁ፡ የአገልግሎት ባልደረቦቼ፡ በዚያ በዓል ላይ የተገኘነው፡ የእርስዎን *"የክብር ተናጋሪነት"* ማዕርግ ለመቀበል ሳይኾን፡ የመንፈስ ቅዱስን መሪ ቃል ተከትለን፡ "ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት" አገልግሎት፡ እኛ፡ በቃል ኪዳን የገባንለትን ዓላማ ለመፈጸም መኾኑን፡ እንደገና ሳረጋግጥልዎ ደስ ያለኛል፡፡ በዚህ መልክ የተገኘን ከኾንን ደግሞ፡ እውነተኛውን የኢትዮጵያዊነት መልእክት ለማድረስ፡ በቦታው በተገኘሁት በእኔ ላይ፡ ያን የመሰለው ተቃራኒ ድርጊት በመፈጸሙ፡ ሊያስደንቀን አይቻልም፤ ምክንያቱም፡ በኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን እንደሚታወቀው፡ የመንፈስ ቅዱስ የኾነውን ሥራ ኹሉ፡ የሚቃወምና ለማፍረስ የሚሞክረው፡ ዲያብሎስ የሚባለው፡ ርኩስ መንፈስ፡ የሐሰት አባትና የክፋት አበጋዝ በመኾኑ፡ ስለኢትዮጵያዊነት እንዲነገር የሚፈልገው፡ ከእርሱ የሚመነጨውን፡ ሐሰት የኾነውን አፍራሽ ነገር እንጂ፡ የእግዚአብሔር በኾነችው እውነት ላይ የተመሠረተውን ገንቢ ቁም ነገር ስላልኾነ ነው፡፡

እንደዚያማ ባይኾን፡ ከእርስዎ ተፈቅዶልኝ፡ በመድረኩ ላይ ቆሜ መናገር በጀመርሁት በእኔ ላይ፡ ያን የሚያህል የአጥቂነት ዘመቻ፡ እንዴት በድንገት ታቅዶ ሊካኼድ ይቻል ነበር? ያን የመሰለ መራወጥና መታወክስ ስለምን ይታይ ነበር? ወይስ፡ ስለበዓሉ ዝግጅትና አመራር፡ ከእርስዎ በቀር፡ ሌላ፡ ባዕድ የኾነ ሥውር የበላይ ኀላፊ ነበረብዎት ብዬ ልጠራጠር? ይህንም የሚያረጋግጠው፡ "በሜዳው ላይ እንድንቆይ፡ ለበዓሉ የተሰጠን ጊዜ አልፏልና፡ የመብራት ኀይሉ ጭምር ሊቋረጥብን ስለኾነ፡ ንግግርዎን ያቁሙልን!" ተብሎ፡ የእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት መልእክቴ፡ ባጭር እንዲቀጭ ከተደረገ በኋላ፡ በረዥሙ ለቀጠለው፡ ለሙዚቃውና ለዘፈኑ ዝግጅት፡ በቂ ጊዜ መሰጠቱ ነው፡፡ ያም እንኳ፡ የኢትዮጵያ ሳይኾን፡ የሱዳን መኾኑ፥ ኢትዮጵያዊነትን የሚያለመልም ሳይኾን፡ ባዕድነትን የሚያጎለብት መኾኑ አያስገርምም? ታዲያ! ይኼን የመሰለው ድርጊት ነው፡ "ኢትዮጵያዊነት"? አያሌ ጊዜያት መላልሰን፡ "ኢትዮጵያዊነት!" "ኢትዮጵያዊነት!" የምንለው "ኢትዮጵያዊነት"፡ እንግዴህ፡ ይኼ ነው? ከዚህ በቀር፡ ለእኔ፡ "አልቋል!" ተብሎ፡ ለሙዚቃውና ለዘፈኑ የዋለው ጊዜ፡ እንደገና ተራዝሞ፡ በተዝናና መልክ ከቀረበው፡ ከእርስዎ የማጠቃለያና የመዝጊያ ንግግርም በፊት፡ ለአንድ ተናጋሪ፡ መድረኩ ተሰጥቷቸው እንደነበረ ይታወሳል፡፡ መድረኩ፡ ለእኔ በተፈቀደበት ጊዜ፡ የበኩሌ ዝግጅት፡ መልእክቴን፡ በአጭር አጠቃልዬ ለማቅረብ የነበረ ሲኾን፡ በእርስዎ በኩል፡ ቅንነት ኖሮ ቢኾን፡ 5 ደቂቃም ብትኾን፡ "የተሰጠህ ጊዜ፡ ይህን ያህል ነው" ተብሎ፡ በቅድሚያ ሊነገረኝ በተገባና ያም ኹሉ ችግር ሊወገድ በተቻለ ነበር፡፡

እርስዎ እንደጻፉት፡ እኔ፡ በዚያ በዓል ላይ የተገኘሁት፡ በእውነት፡ በ*"ክብር ተናጋሪነት"* ከኾነ፡ ታዲያ፡ ከሌሎቹ የክብር ተናጋሪዎችዎ የተለየ፡ ያ ኹሉ አሳዛኝ ድርጊት፡ በእኔ ላይ ለምን ተፈጸመ? ለመኾኑ፡ ላንድ *"የክብር ተናጋሪ"* ሊፈጸም የሚገባው ኢትዮጵያዊ ሥነ ምግባር ነበርወይ፡ ለእኔ የተደረገው? ጠርተዋቸው የቀሩብዎ የክብር ተናጋሪዎችዎ መጥተውልዎ ቢኾን ኖሮ፡ በእኔ ላይ የደረሰውን ሊመስል ይችል ነበርወይ፡ ለእነርሱ የሚያደርጉላቸው? እንደዚያ እንደማይኾንማ፡ ለተገኙልዎ *"የክብር ተናጋሪዎች"*፡ -ፀረ ኢትዮጵያዊነት አቋም ያላቸው መኾናቸው እየታወቀ ለተጋበዙት ሳይቀር- የመናገሪያ መድረኩን፡ በበቂ ጊዜና መዝናናት እንዲጠቀሙበት ከማበርከት ጋር፡ በወጉ የተደረገላቸውን አቀባበልና አያያዝ፡ በዚያ የነበረው ኹሉ ተመልክቶታል፡፡

እኔ፡ ያለልዩ ጥሪ፥ የአገልግሎት ባልደረቦቼም፡ በፈቃዳቸው፡ እዚያ የተገኘነው፡ ከላይ እንደጠቀስሁት፡ የማንነታችን መታወቂያ የኾነውን፡ "እውነተኛ ኢትዮጵያዊነትን" በይፋ አረጋግጠን ለማሳወቅ፥ "ስለኢትዮጵያዊነት" ተገቢውን አገልግሎት ለመፈጸምና አስፈላጊ ከኾነም፡ ማናቸውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል፡ ዝግጁነታችንን ለመግለጽ ስለነበረ፡ በእኔ ላይ የተካኼደውን፡ ያን የመሰለ አደናጋሪ ድርጊት፡ ከቁም ነገር ሳልቆጥር፡ የኼድሁበትን ግዳጄን፡ በእርጋታና በአግባቡ አከናውኜ መመለሴን፡ የራስዎ ምስክርነት ይበቃኛል፡፡ በተለይ፡ በመጨረሻ ለተደመጡት "የክብር ተናጋሪዎ"፡ እርስዎ የሰጧቸውን ወሰን ያልነበረውን የንግግር ጊዜ፡ በእኔ ላይ ከደረሰው ተቃራኒ ኹኔታ ጋር ሲያመዛዝኑት፡ "እውነተኛ ኢትዮጵያዊ" ከኾኑ፡ ያ፡ ኢትዮጵያዊ ሕሊናዎ፡ ከቶ ምን አለዎ? ዛሬስ ምን ይልዎታል? ያን ደብዳቤ እንዲጽፉልኝ ያስገደደዎ፡ ይኸው ሕሊናዎ ይኾን? ወይስ፡ በዚያች የጥቂት ደቂቃዎች ጊዜ በሰጠሁት ትምህርት፡ *"ብዙ ሰው መደሰቱን አውቀናል፤"* ሲሉ፡ በደብዳቤዎ ውስጥ የጠቀሷቸው አድማጮች፡ የኋላኋላ ከሰጡዎ አስተያየት የተነሣ ሊኾን ይችላል ብዬ ልገምት? በዚህ ረገድ፡ የደረሱትን ኹኔታዎች በመመልከት፡ እኔና የአገልግሎት ባልደረቦቼ፡ በእርስዎ በኩል የነበረውን፡ ያዚያን፡ "የኢትዮጵያዊነት ቀን" በዓል ዓላማ፡ እንዳሰብነውና እንደመሰለን ኾኖ እንዳላገኘነው ልሸሽግዎ አልፈልግም፡፡

ታዲያ፡ ነገሩ እንዲህ መኾኑን፡ እርስዎም፥ እኔም እያወቅነው፡ እርስዎስ፡ ራስዎን፡ ምን ዓይነት ኢትዮጵያዊ አድርገው ነው፥ እኔንስ፡ በምን ገምተውኝ ነው፥ ይህን የመሰለውን፡ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ ቃል አክለው ሊጽፉልኝ የደፈሩት!? እንደርስዎ ግምት፡ ይህን የደብዳቤዎን ቃል፡ ዝም ብዬ ተቀብዬው፥ ወይም ይሉኝታ ይዞኝ አሳልፌው ቢኾን ኖሮ፡ ከንቱ ውዳሴን የምፈልግ ባስመሰለኝ ነበር፤ እርስዎም ሳይቀሩ፡ ሳይታዘቡኝ የሚቀሩ አይመስለኝም፡፡

...4

መቼም፡ ይህ የከንቱ ውዳሴ ረቂቅ ደዌ፡ “መንፈሳውያን ነን” በሚሉ የሃይማኖትና የቤተ ክህነት ሰዎች ላይ ሳይቀር፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ፡ እጅግ ሰፍኖና ተስፋፍቶ ስለሚታይ፡ “እርሱንም ሳይጠናወተው አይቀርም!” ብለው አስበው ይኾናል፤ እንዲህ አስበውኝ ከኾነ፡ ተሳስተዋል። እንደዚያ ያለሁ ሰው ብኾንማ ኖሮ፡ ከኹሉ በፊት፡ “ኢትዮጵያዊ” ተብዬ ልጠራ ባልተገባኝ ነበር፤ ከዚህም ጋር፡ ባሁኑ ጊዜ፡ የምጋደልለትንና እርስዎ ሳይቀሩ፡ “በኢትዮጵያ ቀን”፡ በክብር ተናጋሪነት ሊጋብዙት ያልፈለጉትን፥ በነፋስ ድምፅዎም ላይ ለቃለ መጠይቅ ሊያቀርቡት የፈሩትን፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነትን አቋም ይገፔ የምገኝ ባልኾንሁ ነበር፤ ዛሬም ለእርስዎ የሰጠሁትን፡ ይህን የመሰለውን ግልጽ ምላሽ ባልጻፍሁልዎ ነበር። እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ አገልጋይ ነኝ እንጂ፡ የሰዎች መንግሥት፥ ወይም ድርጅት፥ ወይም ዓላማ አገልጋይ አይደለሁም፤ ስለዚህ፡ የምመራው፡ በእግዚአብሔር የእውነት መንፈስ ብቻ ነው።

ያ ኹሉ ድርጊት ለተፈጸመብኝ ለእኔ፡ “በክብር ተናጋሪነት ተገኝተው” ብሎ፡ እውነቱን በሓሰት ለውጦ መጻፍ፡ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ሳይኾን፡ ከአስመሳዮችና ከዘመኑ የሥነ መንግሥት ፈሊጠኞች የሚመነጭ አሳብ ስለኾነ፥ ይህን የመሰለውም አስተሳሰብና አድራጎት፡ ከፀረ-ኢትዮጵያዊነት ተለይቶ ሊታይ ስለማይቻል፡ አልቀበለውም። ይህን ትውልድ፡ ዛሬ ካለበት፡ አሳዛኝ ውድቀት ያደረሰው፡ ይኸው አካኼዱ በመኾኑ፡ ጤናማና ሰላማዊ ህልውናውን እንደገና አግኝቶ፡ የብልጽግናና የሥልጣኔ ዕድገቱን ይቀጥል ዘንድ፡ ይህን፡ የዲያብሎስ የኾነውን መርዘኛ ጠንቅ፡ ከሥሩ መንግሎ ሊያስወግደው የሚገባ መኾኑን፡ እርስዎን ለመሰሉ ታዳጊ የኢትዮጵያ ልጆች፡ አበክሬ ማሳወቅን አልተውም።

ከኹሉም ይልቅ፡ ለሥራዎ፡ መታወቂያ ያደረጉት፡ “ኢትዮጵያዊነት” የሚለው ስያሜ፡ ለማንም ሰው፡ ቀላልና ተራ ነገር መስሎት፡ በፈለገው መንገድ ሊተረጒመውና ወደፈለገው አግጣጫ ሊወስደው፥ ለፈለገው ባዕድ ዓላማም ሊያውለው የማይቻለው መኾኑን፡ ደግሜና አጠንክሬ ላሳስብዎ እወድዳለሁ፤ ምክንያቱም፡ ከላይ እንደጠቀስሁት፥ በመጻሕፍቴም እንዳመለከትሁት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ደም ታትሞ፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በቃል ኪዳን የተዋሃደ፥ ዘለዓለማዊ የሕይወትና የህልውና ስያሜ በመኾኑ ነው። ስለዚህ፡ በእርስዎ በኩል፡ ስለ“ኢትዮጵያዊነት” በሚያስቡት፥ በሚናገሩትና በሚጽፉት፥ እንዲሁም በሚያደርጉት ኹሉ፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ማስቀደምን እንዳይዘነጉ፥ እንዲህ ካልኾነ ግን፡ የሚያስከትለው ፍዳ፡ በመለኮታዊነቱ፡ ከባድ መኾኑን እገልጽልዎ ዘንድ፡ ኀላፊነቴ ይጠይቀኛል።

ይህን ለማለት ያስገደደኝ፡ “ኢትዮጵያዊነት” ለሚለው አምላካዊ ቃል፡ ያለዎትን ፍቅርና ቅንዓት፡ በጥረትዎ ስላየሁ ነው። ይኹን እንጂ፡ ያደረብዎት ፍቅርና ቅንዓት፡ ለየትኛው ዓይነት “ኢትዮጵያዊነት” እንደኾነ፡ ለይቼ ለማወቅ፡ በተለይ፡ ከበዓሉ በኋላ፡ ለእኔና ለባልደረቦቼ የተሳነን መኾኑን፡ ሳልጠቁምዎ አላልፍም። መቼም፡ “ኢትዮጵያዊነት”፡ አይለወጥም፤ አንድ ነው። ያም፡ እግዚአብሔር የመሠረተው ነው፤ እርሱም፡ አማናዊው፡ ማለትም፡ “እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት” ነው። በዚህ አንጻር ደግሞ፡ አስመሳዩ፡ ማለትም፡ “ሓሰተኛው ኢትዮጵያዊነት” አለ። ታዲያ፡ እርስዎ፡ ይህን “የኢትዮጵያዊነት ድምፅ” የሚለውን፡ ነፋስ ድምፅ ሲወጥኑ፡ የየትኛውን “ኢትዮጵያዊነት” ዓላማ ለማራመድ አቅደው ኖርዋል? በዲያብሎስ የሓሰት አሸዋ ላይ የቆመውን፡ “አስመሳዩን ኢትዮጵያዊነት”? ወይስ፡ በእግዚአብሔር የእውነት ጭንጫ ላይ የተመሠረተውን፡ “አማናዊዉን ኢትዮጵያዊነት”? መቼም፡ “ኢትዮጵያዊነት” ሃይማኖት ነውና፥ የሃይማኖት መገለጫውና መታወቂያውም፡ የንስሓ ምግባርና በጎ ሥራ ስለኾነ፡ የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ፡ መሪያችን፡ “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ!” ያለውን ቃል በመከተል፡ ከእርስዎ የንስሓ ምግባርና ከነፋስ ድምፅዎ የሥራ ፍሬ እንጠብቃለን። እርስዎና እኔ፡ በመታደልም ኾነ፡ ባለመታደል፡ የምንገኝበት፡ ይህ ትውልድ ግን፡ “እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት” ሊለውጥ፡ ሙከራውንና ጥረቱን እየቀጠለበት ስለኼደ፡ እነሆ፡ እየተሠቃየበት የሚታየውን መከራ እንመለከታለን። በዚህ ረገድ፡ እርስዎም፡ ያለብዎትን ኀላፊነት እንዳይዘነጉትና እንዲጠነቀቁበት የሚያስፈልግዎ መኾኑን ማሳሰብ፡ የእኔም ግዴታ ይመስለኛል።

...5

ምን ጊዜም እንደማይለየን የምናምነው፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በዚህ ጉዳይ፡ ከዚያች “የኢትዮጵያ ቀን” ጀምሮ፡ እየሠራ መቀጠሉ፡ በእኛ፡ በቃል ኪዳን ኢትዮጵያውያኑ ዘንድ የተረጋገጠው፡ ዕለቱ የእርሱ በዓል የዋለበት መኾኑ ብቻ ሳይኾን፡ 1ኛ:- በስሙ የምናገለግለውን፡ እኛን፡ በዚያ በዓል ላይ እንድንገኝ ማድረጉ፥ 2ኛ:- እዚያም፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ላይ፡ ቀደም ብሎ የተነገረውን የተዛባና ሓሳዊ አስተሳሰብ ለማስተካከልና ለማቃናት እንድችል አድርጎ፡ የንግግሩን ዕድል፡ በግዳጅ፡ ለእኔ መስጠቱ፥ 3ኛ:- በዚያን ቀን፡ በእርሱ የተቀደሰ ዓላማና አገልጋዮቹ ላይ የተፈጸመው፡ ያ ኹሉ አሳዛኝና አስተዛዛቢ ድርጊት፡ ተድበስብሶ ሳይቀር፡ በግልጽ ይታወቅ ዘንድ፡ እርስዎ፡ ይህን ደብዳቤ እንዲጽፉልኝና እኔም ይህን የተብራራ ምላሽ እንድሰጥዎ ማስገደዱ ናቸው:: ስለዚህ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ከኾኑ፡ ለእኔ የጻፉትን ደብዳቤ፡ ሓሰቱን በእውነት አርመውና ተክተው ከማስተካከል ጋር፡ በዚያን በዓል፡ በእኔና በአገልግሎታችን ላይ፡ በረቂቅ መንገድ ለተፈጸመው በደል፡ አምላከ ኢትዮጵያን፡ በንስሓ ይቅርታ መጠየቅ እንደሚገባዎት ልመክርዎ እወድዳለሁ:: የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት፡ ዓይነተኞች ባሕርያት፡ በመንፈስ ቅዱስ እውነትና ግልጽነት፡ ማሰብ፥ መናገርና መጻፍ፥ ማድረግም ስለኾነ፡ ይህ ምክሬና የቀደሙት ማሳሰቢያዎቼ ኹሉ፡ በዚህ መልክ የቀረቡ መኾናቸው ታውቆ፡ ለፍጻሜ እንዲበቁ፡ አደራ ጭምር እጠይቃለሁ::

በደብዳቤዎ መዝጊያ፡ *“ወደፊት በሚኖረው ዝግጅታችንም ኾነ፡ በጋራ ጉዳዮቻችን ላይ፡ አብረን እንደምንቆም፡ ተስፋችን ሰፊ ነው”* ሲሉ ያሠፈሩት መልካም ቃል፡ ተፈጻሚነት የሚኖረው፡ እርስዎና ነፉስ ድምፅዎ፡ “የእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት” ወገንነታችሁን፡ በትክክል ሲያሳውቁንና እኛም አውቀን ስንቀበለው መኾኑን፡ አስቀድሜ ስገልጽልዎ ደስታ በተመላበት ተስፋ ነው:: ከዚህ ግብ ለመድረስ፡ “ኢትዮጵያዊነት” የሚጀምረው፡ ከራስና ከቤት ስለኾነ፡ በቅድሚያ፡ ራስዎን፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ማብቃት፥ ነፉስ ድምፅዎም፡ ለዚሁ፡ የእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ዓላማ እንዲያገለግል የቆመ መኾኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይኾናል:: በዚህ ረገድ፡ ከእኔና ከአገልግሎታችን የሚፈለግ እርዳታና ድጋፍ ቢኖር፡ ይህንኑ ለማበርከት ዝግጁዎች ነን:: የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱን ብቅዓት፡ ለራስዎ፥ የብቅዓት አገልግሎቱንም፡ ለድርጅትዎ አስገኝተው ከኾነ፡ “እንኳን ደስ አለዎ!” እያልሁ፡ የዚህን ማረጋገጫ እጠብቃለሁ:: ከዚህ ጋር፡ በደብዳቤዎ ላይ የሠፈሩትና በነፉስ ድምፅዎ የሚደመጡት፡ የሰዓት፥ የቀንና የዘመን አቆጣጠሮች፡ የራሳችን በኾኑት፡ የኢትዮጵያ አኀዛትና ስሌታት ይኾኑ ዘንድ፥ ያም ባይኾን፡ ቅድሚያው፡ በማናቸውም ረገድ፡ ከባዕዳኑ ይልቅ፡ ለኢትዮጵያዊው ሥርዓት ይሰጥ ዘንድ፥ ቋንቋችንና የሥነ ጽሑፋችን ሆህያትና አኀዛትም ይጠበቁ ዘንድ እንደሚገባ፡ በዚህ አጋጣሚ አሳስብዎታለሁ::

ይህን ኹሉ መጻፌ፡ የኢትዮጵያዊነት አቋምዎን፡ በእግዚአብሔር እውነት እያጠሩና እያጠናከሩ እንዲኼዱ ላበረታታዎ እንጂ፡ በግልጽ መማማርንና መተራረምን የማይፈልጉ፥ ራሳቸውን ግን፡ “ኢትዮጵያውያን” ብለው የሚጠሩ ወገኖች፡ በማጣመም እንደሚተረጕሙት ከዓላማዎ ላዳክምዎ፥ ወይም ተስፋ ላስቆርጥዎ አለመኾኑን እንደሚገነዘቡልኝ አምናለሁ:: ለዚህም፡ በማቴ. 7፥ "4-"7 ላይ የተጻፈውን፡ የመሪያችን የኢየሱስ ክርስቶስን አጭር መመሪያ ቃል፡ በመንፈስ ቅዱስ ልቦና ኾነው ይመለከቱት ዘንድ ጠቅሼልዎታለሁ::

ጥረትዎና ትግልዎ፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ይኾን ዘንድ፡ አምላከ የኢትዮጵያ፡ በጸጋውና በረድኤቱ እንዲመራዎ እንጸልያለን::

---

ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ (ንቡረ እድ)
ዋና አገልጋይ